# የከዘራው ትንቢት አልተፈጸመም እንዴ?

ይሄይስ አዕምሮ

ትናንት ማታ የድረ ገጽ ዜናዎችን ሳነብ ያየሁት አስገራሚ ዜና በሌላ ጉዳይ ላይ ልጽፍ ተነሳስቼ የነበርኩትን ሰውዬ ወዲያውኑ አስለወጠኝ - ብቻየን በሳቅ ስንከረከር የራሴው የሳቅ ማሚቶ እንደገና እያሳቀኝ በቶሎ ላቆም አልቻልኩም - አስመሸኝ፡፡ የወያኔው ገልቱ ሥርዓት እንዴቱን ያህል  የወዳጆቹን ብቻ ሳይሆን የጠላቶቹን ጭምር አንጀት በሚበላ አሳዛኝ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ስገነዘብ እኔ ራሴም ሆዴን ባር ባር አለው - ክፉኛ ተንቦጫቦጨለት - ሲያልቅ አያምር አሉ፡፡ የምሬን ነው፡፡ «አትፍረድ ይፈረድብሃል» ነውና በሰው ጭንቀት እንዳናላግጥ አደራችሁን፡፡ ወያኔ በጣም አሳሳቢና አስከፊ የጎልውና ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ አሁን ማን ይሙት ወያኔ ባይጨነቅና ባይጠበብ ኖሮ የረር ገዳም ውስጥ ገብቶ «ባለከዘራውን ንጉሥ ውለዱት፤ አለበለዚያ ሁላችሁንም እጨርሳችሁዋለሁ!» ብሎ መናንያንንና ምዕመናንን ሊፈጅ ፌዴራል ያዘምት ነበር? አንድ የ21ኛው ክፍል ዘመን ሊያውም በ99.6 በመቶ ድምጽ በሕዝብ የተመረጠ ሥልጡን መንግሥት እንዴት ወደዚህ የምርኩዝና የከዘራ ትንቢት ይወርዳል? ይሄ መንግሥት ያላሳዘነ ማን ሊያሳዝን ነው ታዲያ? የሚያፍር ዜጋ  ካለ በዚህ የህዝብ መንግሥት ያላፈረ በሌላ በምን ሊያፍር ይችላል? ጊዜ አግኝታችሁ ብታስቡት እኮ በርግጥም ያስገርማል፤ በሀፍረትም ያሸማቅቃል፡፡

ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በብሉይ ኪዳን ነቢያት ቀደም ሲል በዚያን ዘመን እንደሚወለድ ትንቢት ተነግሮ ነበር፡፡ ጊዜው ሲደርስ በቤተልሔም በበረት ውስጥ ተወለደ፡፡ ይህን ትንቢት የተረዱ ሦስቱ ሰብዓ ሰገል በኮከብ ምሪት የዓለም መድሐኒት ወደተወለደበት አገር ገጸ በረከት ይዘው መጡ፡፡ ግን የግዛቲቱን ንጉሥ ፈቃድና የጉብኝት ይሁንታ ለማግኘት ፈልገው ወደቤተ መንግሥት ለመግባት መሻታቸውን መንፍስ ቅዱስ  ባወቀ ጊዜና ኮከቡ ተሰወጠባቸው - ወዳሳቻ ሥፍራ ተሠወረባቸው፡፡ ነጉሡንም አሉት - « ንጉሥ ሆይ በግዛትህ የአይሁድ ነጉሥ ይወለዳል የሚለውን ትንቢት አንብበን ልንጎበኘውና ስጦታም ልናበረክትለት በኮከብ ምሪት እዚህ ግዛትዎ ብንመጣ ይመራን የነበረው ኮከብ ተሰወረብን፤ እባክዎን ያፈላለጉልንና የልባችን ይድረስ. . .፡፡» የዚህን ጊዜ ንጉሡ ተደናገጠ፤አለቅጥም ተርበተበተ፡፡ በግዛቱ ሌላ ነጉሥ መወለዱ በቅናትና ምቀኝነት አንገበገበው፤ ዙፋኑን ከነበትረ መንግሥቱ ሲያስረክብ እየታየው፡፡ ነቢያቱንና ዐዋቂዎችን ሁሉ አስጠራ፤ ሰበሰባቸውምና «የዚህን ሕጻን ጉዳይ

ዕልባት ካልሰጣችሁኝ ከዚህ ቦታ ውልፊት የለም» አላቸው:: ተጨነቁ፣ተጠበቡ:: መጻሕፍትን አገላበጡ፣ ሁሉም በየፊናቸው የአቅማቸውን ተፍጨረጨሩ፣ የሆነላቸው ነገር ግን አልነበረም:: በመጨረሻ ንጉሡ እንግዶቹን እንዲቀናቸው «ጸልዮ» «በሉ በራሳችሁ መንገድ ያን የተከበረ የአይሁድ ንጉሥ ፈልጉት፣ ስጦታችሁንም አበርክቱለት: ተመልሳችሁ ግን ቦታውን ለኔም አሳዩኝ፣ እኔም የበኩሌን ታላቅ የሆነ ንጉሣዊ ስጦታየን አበረክትለታለሁ» ብሎ አሰናበታቸው:: ሰዎቹ ከቤተ መንግሥቱ እንደወጡ ለነሱ ብቻ የተላከው ኮከብ ምሪቱን ቀጠለ:: ቦታው ላይም ያላንዳች መደናገር ደረሱ፣ ለእምቦቀቅላው ሰገዱለት፣ ያመጡለትንም ስጦታ ሰጡ:: ሲመለሱ ግን ወደ ንጉሡ እንዳይመለሱ ኮከቡ በሌላ መንገድ ወዳገራቸው ይዞኣቸው ነጎደ::

ለዜናው ብሥራት የእንግዶቹን ወደቤተ መንግሥት አለመመለስ የተረዳው ንጉሥ ሄሮድስ(የኛው መለስ መሆኑ ነው) ሆን ብለው እንዳታለሉት በመቁጠር በንዴት ፎገላ:: «ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት» አስባለና የጦርነት ከበሮ አስደለቀ:: ሕጻኑ ክርስቶስ ይወለድበታል ተብሎ በተጠረጠረው ቤተልሔምና አካባቢዋ የሚገኝ ዕድሜው ከሁለት ዓመት ያልዘለለ ጮርቃ ሁሉ እየታደነ ከእናቱ አንቀልባና ከአባቱ እቅፍ እየወረደ ለጥይት አረርና ለሠይፍ ተዳረገ:: «ጨኸት በራማ በረከተ፣ራሔልም ስለልጆቹዋ አምርራ አለቀሰች» የተባለለት ትንቢትም ያኔ ተፈጸመ:: (በታሪኩ አቀራረብ ካህናትን ይቅርታ እጠይቃለሁ - በራሴው እንጂ እንደመጽሐፉ አይደለም ያቀረብኩት)

ርዕሰ ወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ሄሮድስ ዜናዊ ከእውነተኛው ሄሮድስ የተለዩ ነገር አላደረገም:: «ግደሉ» ሲባሉ «ስንት?» እንጂ «ለምን?» ብለው የማይጠይቁ ማይማን የጦር አባላቱን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች አሰማርቶ ሕዝብን የሚፈጅ መንግሥት ያላት በተለይ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ብቻ ናት ቢባል ከእውነት አልራቅንም:: በቋንቋ ከሕዝቡ ጋር የማይግባባ፣ በሃይማኖትና በገምቢ ኢትየጵያዊ ባህልና ትውፊት ተኮትኩቶና ተቀርፆ ያላደገ፣ ከትምህርት ቤት ሳይሆን እልም ካለ ገጠር ከእረኝነትና ከማሳ ላይ ተለቅሞ የመጣ፣ መሣሪያ ከመተኮስ በስተቀር ሌላ ሥጋዊም ይሁን መንፈሳዊ ዕውቀት እንዳያገኝ ሆን ተብሎ በማይምነትና በጥላቻ ጭምብሎች ዓይኑ እንዲጨነበል የተገደደ ሠራዊት ያላት ብቸኛዋ ሀገር አሁንም ኢትዮጵያ ብቻ ናት:: «እባክህን የዛሬን ማረኝ!» ብለህ ከጠብመንጃ ሠደፍ ወይም ከጥይት ንዳድ እንዲምርህ ስትለምነው በወሰደው የተንኮለኞች ሥልጠና ሳቢያ እንደስድብ እንዲቆጥረውና አስቀያሚ ርምጃ እንዲወስድብህ የሚደረገው ኢትዮጵያ

ውስጥ ብቻ ነው:: «በናትህ» ሲሉዋቸው «እናትህን ማለት ነው»፤ «እህት ወይ ወንድም የለህም?» ሲሉዋቸው «በጣም መጥፎ ስድብ» ስለሆነ በምንም መንገድ እንዳይለቁዋቸው ለማይማን የሠራዊት አባላት ሥልጠና የሚሰጥባት በዓለም የመጀመሪያዋ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ናት::

የሰሞኑ ዜና ደግሞ ከእስከዛሬው ሁሉ የተለዬ ነው:: ከጥንት ጀምሮ የሚባል አንድ ትንቢት አለ:: ብዙዎቻችን እናውቀዋለን:: ሌሎችም አሉ በርግጥ:: ዘመኑ በግልጽ አልተነገረም እንጂ ከብዙ ሀገራዊ ትርምስና ሁከት በሁዋላ «በምሥራቅ በኩል የሚመጣ ስሙም ቴዎድሮስ የሚባል በከዘራ/በምርኩዝ ኢትዮጵያን የሚገዛ ንጉሥ» እንደሚነግሥ በአንዳንድ ባህታዉያን በልጅነት ጊዜየ ሲነገር እንደነበር አስታውሳለሁ:: እንዲያውም በቅርቡ በዚሁ በወያኔ ጊዜ አንድ ስብሰባ ላይ አንድ ጳጳስ ይሁን ቀሲስ አቶ መለስ በሚመራው የንቃት ማዳበሪያ ስብሰባ ላይ በስሜት ብድግ/ቱግ ብሎ « እርስዎ ትንቢት የተነገረለትና በየረር በኩል የሚመጣው - እንደ ሙሴ በከዘራ ብቻ የሚመራው ንጉሥ ነዎ፤ዕድሜዎን የማቱሳላ ያድርግልንና . . .» እያለ ሲወሻክት መለስም በሳቅ ሲንከተከት አስታውሳለሁ:: በትንግርተኛዋ ሀገራችን ምን የማንሰማውና የማናየው ነገር አለ መሰላችሁ? እኔም እንደዚያ ነው የማምን ለነገሩ:: እኔ የምለየው ግን የመለስ ከዘራ ውስጥዋ የያዘው እንደጆን ዎከር ዊስኪ ወይም ጠንባሆና አደንዛዥ ቅራቅንቦ ብቻ ሳይሆን ባሰኛት ሰዓትና በፈለገችው ሰው ግምባር ላይ የምትረፈርፈው ጥይት ነው:: የመለስም አመጣጥ ከኔው ከሰሜነኛው የሚመደብ እንጂ ከፀሐይ መውጫ አይደለምና «ምሥራቅ»የምትለዋ ቃለ ትንቢት አታስኬድም:: ስለዚህ የቀባጩ ሆድ አደር የቄሱም ሆነ የኔ የጨዋው ተፍጻሜተ ትንቢት ግምገማ አይሠራም ማለት ነው::

በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ትንቢቶች ይነገራሉ፤ ከእውነትም - ከቅዠትም - ከውሸትም - ለማደናገሪያነትም ሆነ ለሌሎች ዓላማዎች ሲባል:: በጫካ ውስጥ ያሉ ቅጠላ ቅጠሎችንና ሥራ ሥሮችንም ማመን አስቸጋሪ ነው:: ጉሽ ጠላና ቁንድፍት እንኩዋን ባቅማቸው የስንትና ስንት ትንቢቶች አመንጪ ባለውለታዎቻችን አይደሉ እንዴ? ሰው ሲጨነቅ መተንበይ አይደለም «እኔ የትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜ የሆንኩ ክርስቶስ ኢየሱስ ነኝ» ብሎ ራሱን አምላክ አማልክት እስከማድረግ ይደርሳል - በተለይማ በዚህ እላቂ ዘመን የሚታየው ጉድ ልዩ ነው:: ሁነኛውን ከአስመሳዩና ከማጭበርበሪያው የመለየት ኃላፊነት ታዲያን የአድማጩና የትንቢት ተርጓሚው ነው መሆን ያለበት - በተለይ

በዚህ አስጨናቂና አብዶ የሚያሳብድ ወቅት መጠንቀቅ አይከፋም፡፡ «በዚህ መጣ፤ በዚያ ሄደ ቢሉዋችሁ አትመኑ፤ የጊዜው መገለጫ ነው» ተብሎ ቀድሞዉኑ በመጽሐፉ ተጠቁሞኣልና እንደናገጥ ነው የምል፡፡

ሁነኛ ትንቢቶች አሉ ብለን እንኩዋን ብንቀበል አብዛኞቹ ትንቢቶች በገደምዳሜና በይሆናል ስለሚነገሩ የሚፈጸሙብትን ዘመን በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ በስመ ትንቢት ደግሞ ብዙ ነገር አለ፡፡ አድማጭ እንዲያገኝ የሚፈልግ ምድረ ባህታዊ ነኝ ባይ በዐውደ ምሕረት ቆሞ ወይም በቤተ ክርስቲያን ቅጥረ ግቢ ካብ ተጠግቶ የሚወሻክተውን ሁሉ ትንቢት ነው ካልን የወያኔን ዕድሜ ቢያንስ በምናብ ደረጃ ለማሳጠር እሁድ እሁድ ወደሚቀርበን ቤተ ክርስቲያን መሄድ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ አንዳንድ «ነቢዮች» የሕዝቡን ስሜት በሚገባ ስለሚያውቁ በቁስሉ ይገቡበታል፡፡ እናም ምን ሊሉ ይችላሉ? « አዎ! ምዕመናን፤ እኔና እናንተን እዚህ ያሰባሰበን የሠራዊት ጌታ እግዚኣብሔር በኔ በባሪያው አማካይነት እንዲህ ብሎኣችሁዋል፡፡ ዕንባችሁን አብሳለሁ፤ ደማችሁን እመልሳለሁ፤ ፀሐዩን ንጉሥ በምሥራቅ በኩል አምትቼ አነግሥላችሁዋለሁ፡፡ ጊዜው ቀርቦኣል፡፡ ጊዜው የናንተ ነው ሕዝበ ክርስቲያን! እልል በሉ እንጂ ምዕመናን! . . .» ከዚህ በሁዋላስ ምን ሊል ይችላል? « አዎ - ምዕመናን መቼም ያለናንተ ተራዳዒነት የሚሆን ነገር እንደሌለ ታውቃላችሁ፤ ተልባማሻ ማርያም የምትባል ገዳም አለች፡፡ የሚበራ ጡዋፍና የሚጨስ ዕጣን እንኩዋን ጭርሱኑ የላትም - እናንተን የመሳሰለ ሕዝበ ክርስቲያን እያለ ድንግል እናታችን ቅዳሴዋ ይታጎል? ቤተልሔሙዋስ ይዘጋና የአውሬ መፈንጪያ ይሁን? አይደረግም! አዎ፤ እናንተም አታሳፍሩኝም - አውቃለሁ፡፡ በሉ የተቻላችሁን ያህል እዚህች ምንጣፍ ላይ ጣል ጣል አድርጉ፡፡ ለበረከት ነው - ለናንተው ነው ለማንም አይደለም፤ እኛማ አንዴውኑ እላይ ነው ዋጋችንን የምናገኘው፡፡. . .» ስለነዚህ ዓይነቶቹ የቅጥፈትና የመክፈልት መብያ ሃሰተኛ ነቢያትና ትንቢቶች ብዙ ማለት ይቻላል፡፡ ግን ይቅርብን- ዋናው በምንሰማው ትርኪ ምርኪ ሁሉ አንወሰድ ነው እኔ የምል፡፡ በነገራችን ላይ እኔ በሰይጣናዊ ትንቢትና በሃሰተኛ ነቢያት እንጂ የማላምን በእውነተኛ እግዚአብሄር ቃልና ትንቢት አምናለሁ፤ ወድጄን? እናም እያላገጥኩባቸው ያለሁት ዉሸታሞቹንና ለከርሳቸው አድረው ፈጣሪንና ሕዝብን የሚያጭበረብሩትን ነው፡፡ ሌላ ታርጋ ትለጥፉብኝና አደራችሁን እንዳትኮነኑብኝ ወገኖቼ - የናንተን እንጂ የነሱንስ ቅዋሜ እችለዋለሁ፡፡ እኔም ቅቤ እየቀባሁዋቸው እንዳልሆነ ይሰማኛል፡፡

በዚህ አጋጣሚ ግን የሀገራችንን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታዎች በጥልቀት ስንታዘብ ብዙ ተስፋ አስቆራጭ እንከኖች የመታየታቸው ነገር በብርቱው ሊያሳስበን እንደሚገባ ልጠቁም እወዳለሁ:: በተለይ በትምህርት ብዙም ያልገፋውን ሕዝባችንን ከነዚህ ድጦች አውጥተን የዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤት ለማድረግ፣ በሕዝብ ቀጥተኛ ተሣትፎ በሚገነባ  የሥልጡን ዘመናዊ ፖለቲካ ተቋዳሽና የእውነተኛ ሃይማኖት መሪዎች ምዕመን እንዲሆን፣ ከአፍዛዥ አደንጋዦች የቁጭ በሉ ፖለቲከኞችና የሃይማኖት ሰዎች መንጋጋ ወጥቶ የዘመነ ስብዕና እንዲላበስ ትልቅ ትግል ይጠብቀናል- ለዚህ የማይቀርልን ሀገራዊ ተግባር ደግሞ በተለይ የዲያስፖራው አስተዋፅዖ ከሁሉም የላቀ ስለሚሆን በያላችሁበት በቂ ዕውቀትና ልምድ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር እንድተቀስሙና ከወዲሁ ዝግጅትም እንድታደርጉ የዜግነት ሃሳብን እንደልብ የመግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን ተጠቅሜ ግለሰብዓዊ ጥሪየን ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፤ ደግሞ ይችን መናገር እንኳዋን ልከለከል ነው- አዎ- አላፍርም አሁንም በድጋሚይህንኑ ጥሪየን አስተላልፋለሁ:: ለሁለንተናዊ ለውጥ ካልተዘጋጀንና በኅበዝ አለቃም ቢሆን እየተደራጀን ለህልውናችን ራሳችን መላ መትተን ካልተንቀሳቀስን አሁን በሚታየው አካሄድ የቀጠልን እንደሆነ የዛሬ 1000 ዓመትም ቢሆን  አሁን ከምንገኝበት ሁኔታ ስንዝር አንራመድም:: ሰዎቻችን በፖለቲካውም በሃይማኖቱም ኮድኩደው ይዘውናል:: በ«ሰማይ አይታረስ፤ ንጉሥ አይከሰስ» ነባር ብሂል ተቀፍድዶ ለዘመናት አሣሩን ሲያይ የነበረው ሕዝብ አሁንና ዛሬም ከዚያ ዓይነቱ የቆዬ ኅታች ይትበሃል አልተላቀቀም:: የፖለቲከኞችና የሃይማኖት መሪዎች የማይነጥፍ ጥገትና የዕብለት ዒላማ የሆነ ሕዝብ ደግሞ በዕድገት ጎዳና ወደፊት ይገሰግሳል ማለት ህልም እንጂ እውን ሊሆን እንደማይችል እስኪያንገሸግሸን ድረስ በተግባር አይተነዋል:: ስለዚህ እንፍጠን ኅበዝ! በጣም ዘግይተናል:: ለጠብና ለሽኩቻ፣ ለአምባጓሮና በዘረኝነት ላይ ለሚመሠረት ማንኛውም ዓይነት ፉክቻ ድንቡሎ ታህል እንኳዋን ጊዜ የለንም::

የትንቢቱን ነገር በተመለከተ በየረፋ በኩል ይመጣል ስለተባለው «ንጉሥ» ብዙ ተብሎኣል፤ መነኮሳት እስኪገደሉና አጸደ ቤተ ክርስቲያን እንደምንጊዜውም ሁሉ እስኪደፈር ድረስ የወያኔው ሄሮድሳዊ ባሕርይ በገሃድ ታይቷል:: እንደኔ እንደኔ መንግሥትም እንደመንግሥት ዝም ብሎ ሥራውን ቢሠራ፣ የሃይማኖት «ነቢያትም» እንዲሁ ሰው የሚጸድቅበትንና ከመጥፎ ድርጊት ተቆጥቦ ሃይማኖታዊ ትሩፋት የሚያገኝበትን መንገድ ማስተማር እንጂ ባልተጨበጠ ነገር ሕዝብን በቀበሮና በተኩላ ባያስጨርሱ፣ ምዕመናንም ብሂሉ « ሽልም ከሆነ ይገፋል፤ ቂጣም ከሆነ ይጠፋል »

እንዲል ትንቢቱ ዕውነትም ከሆነ ባለከዘራው መሪ ይመጣል ካልሆነም ፈጣሪ የሚፈቅደው ነገር እስኪሆን በጸሎትና በምህላ ፈጣሪን እየለመነ በትዕግስት ቢጠብቅ፣ ሁነኛ የነጻነት አርበኞች ወደተገቢ ቦታቸው ሲመጡም - መምጣታቸው የማይቀር መሆኑን ስለምገነዘብ ነው- በነሱ አመራር ወደደገኛይቱ መልካም ዘመን ለመሸጋገር መሞከር እንጂ አሁን ከጎልያድ ጋር አጉል መስዋዕትነት ባይከፍል፣ ወታደሩም ከአውሬነት ወጥቶ እንደሰው ማሰብ ቢጀምርና ጃዝ በተባለ ቁጥር ዜጎችን እየረፈረፈ ሌላው ይቅርና በሠለጠነው ማኅበረሰብ ዘንድ የሀገራችንን ስም በማጉደፍ በዚህ የባርቤሪያን ሥርዓተ መንግሥት ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ምክንያት በውጭ የሚኖሩ ዜጎቻችን በየሚሄዱበት ባይሳቀቁ . . . ዋና ምኞቴ ነው፤ ምኞት መቼስ አይከለከል:: እንጂ ለትንቢት ለትንቢቱማ እኔስ እንዳቅሚቲ የሰማሁዋትን «የአንድ ማሳ እህል ላገር የሚበቃበት ዘመን፤ የአንድ ላም ወተት ተጠጥቶ የማያልቅበት ውብ ጊዜ፤ ሰው ከፍቅር በፍቅር ስለፍቅር የሚፈቃቀድበት ወርቃማና ደግ ዘመን. . .» በግምባር እንደሚመጣ መናገሩ ከብዶኝ ነው እስከአሁን ዝም ያልኩት? አይደለም! «ወርደን እናየዋለን» ብዬ እንጂ:: ነገሬን በዚች ታሪክ ለቋጭ እንግዲያውስ - እመት ጦጢት ዛፍ ላይ ተቀምጣለች:: ገበሬው ቆላ ወርዶ ባቄላ ይሁን አተር ዘርቶ ይመለሳል:: ጦጢት ሆዬ « ገበሬ ምን ዘርተህ መጣህ?» ትለዋለች:: ገበሬው ምኑ ሞኝ - ጦጢት ጥያቄዋን ጠይቃ ከመጨረስዋ «ተልባ!» ይላታል፤ ከተዘራ ማሳ ተልባ እንደማትለቅም ስለሚያውቅና ጦጢትን በመሸወዱም ውስጡን ደስ እያለው:: አጅሪት የዋዛ አልነበረችም - እናም አለችው « አሃ! ጥሩ ነው፤ ወርደን እናየዋለና!» እኛም ትንቢቱንም ሆነ የወያኔን ድካ ወርደን እናየዋለን፤ ነገር ግን አይዞን፤ ብዙ ጊዜ አይደለም የቀረው- ጨለማው ሲበረታ በውስጡ ያረገዘውን ብርሃን ማየት አያስቸግርም፤ጨለማ በብርሃን ላይ ባይሰለጥንም ብርሃን በጨለማ ውስጥ ተረግዞ የድቅድቅ ጨለማን የማይደፈር ምሽግ ይገረስሳል፤የዕብሪት ፍላጻዎቹንና ጥሩሩንም ይማርካል:: ያኔ የክፋት ዋሻ ይደረማመሳል፤ እውነትም ከእሥራቷ ትፈታና የሣሜት ዘመን መባቻው ይታወጃል:: ይሁንና ፈረንጆቹ «ነጻ ምሣ የለም» እንደሚሉት በብላሽ ምንም ነገር ለማግኘት አንጠብቅ:: የሆኖ ሆኖ የኛን የቤት ሥራ እንሥራ እንጂ የነሱን ከሞላ ጎደል እየጨረሱ ነውና ብዙም አንፍራቸው- በሠሩት ግፍና በደል ምክንያት ነቀዝ እንዳመሸከው በቆሎ ገለባቸውን የቀሩ አልቅቶችን መፍራት አስተዋይነት የጎደለው አፈግፋጊነት ነው - ያሰቡትን ሁሉ አድርገዋል - የቀራቸውም ያለ አይመስል:: የሀብትና የሥልጣን ጫፍ ላይ ደርሰዋል - አይጠግቡም እንጂ ክፋታቸው:: ከሁሉም ከሁሉም አንዲት ታላቅ ሀገር በሁሉም ረገድ እንድትጠፋ የሌላ አገር

መንግሥት በቅጥረኝነት በመግዛት ጭምር የተቻላቸውን ሁሉ ጥረዋል - ጥረታቸውን አሁንም እንደቀጠሉ ናቸው፤ እርግጠኞች እንሁን ሁሉም የእጁን ማግኘቱ ግን አይቀርም። የዓለም ነገር የሎሚ ተራ ተራ ጉዳይ ነው። ያገራችን ነገር ቢያወሩት አያልቅም ውድ ምዕመናን፤ ባጠፋሁ ይቅርታ፤ ባጎደልኩ ጨምሩበት፤ የተሳሳትኩትን ባድራሻዬ አርሙኝ፤ ለማንኛውም ቸር ይግጠመን።

yiheyisaemro@gmail.com